17ኛ ዓመት ቁጥር 179 2017 ዓ.ም በነፃ የሚታደል




# በውስጥ ገጾቻችን

«በግብር ከፋዮች የሚቀርቡት ቅሬታዎች ፈጣን ምላሽ ማግኘት ይኖርባቸዋል»



ገጽ 3

ከየካቲት ቀን ጀምሮ ሙሉ በሙሉ ስለሚተገበረው ባለልዩ መለያ ደረሰኝ ምን ያህል ያውቃሉ?



ገጽ 4

SCAN IT
& JOIN US
የታክስ እና ጉምሩክ መረጃዎችን በቀላሉ ያግኙ
በ8199 በነፃ ይደውሉ
www.mor.gov.et

# ከ140 ሚሊዮን ብር በላይ ድጋፍ ተደረገ

**በሰሎሞን ደግአረገ**



የገቢዎች ሚኒስቴር እና የጉምሩክ ኮሚሽን ገቢን ከመሰብሰብ ባለፈ ማኅበራዊ ኃላፊነቱታቸውን ለመወጣት 140 ሚሊዮን 800 መቶ አምስት ሺ በብር እና በዓይነት ባለፉት ስድስት ወራት ድጋፍ አደረጉ።

ድጋፉ የተደረገው አንደኛ በደቡብ ወሎ መስተዳደር ዞን ለኮምቦልቻ ከተማ አስተዳደር 22.6 ሚሊዮን ብር የሚገመቱ የግንባታ ግብዓቶች እና ምግብ ነክ ቁሳቁሶችን በከተማ አስተዳደሩ የሚገኙ አቅመ ደካማ ዜጎችን ኑሮ ለማቃናት እና የኮሪደር ልማቱን ለመደገፍ የተደረገ ሲሆን፤ በተመሳሳይ ለቢሾፍቱ ከተማ አስተዳደር የኮሪደር ልማት ማስፈጸሚያ የሚሆን ከ40 ሚሊዮን ብር በላይ የሚያወጡ የግንባታ ቁሳቁሶችን ድጋፍ የተደረገ ሲሆን ለአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ለአቅመ ደካሞች የሚውል የ15.3 ሚሊዮን የሚገመት የምግብና አልባሳት እንዲሁም 6 ሚሊዮን በገንዘብ በድምሩ የ21 ሚሊዮን ብር ድጋፍ ተደርጓል።

ከላይ ከተጠቀሱት ድጋፎች በተጨማሪ፤ በለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ ስር ለሚገኙ አቅመ ደካሞች የቤት ማደሻ የሚውሉ የተለያዩ የግንባታ ቁሳቁሶች እዲሁም አልባሳት እና ጫማዎችን በክፍለ ከተማው በመገኘት በድምሩ የ10.1 ሚሊዮን ብር ግምታዊ ዋጋ ያላቸው ቁሳቁሶችን፤ እንዲሁም በጎፋ ዞን በተከሰተው የመሬት መንሸራተት አደጋ ለተጎዱ ወገኖች ማቋቋሚያ የሚሆን 7.1 ሚሊዮን 700 መቶ 70 አምስት ሺ ብር የገንዘብ እና 8.6 የዓይነት ድጋፍ ተደርጓል። ከገንዘብ እና ከዓይነት ድጋፍ ጎን ለጎን በአዳማ ከተማ አቅም የሌላቸው 18 ዜጎችን ቤት ገንብቶ አስረክቧል። ከዚህ ባሻገር፤ ለኢፌዲሪ አየር ኃይል የሠራዊት መኖሪያ ቤት ግንባታ የሚሆን ከ32 ሚሊዮን ብር በላይ የሚያወጡ የግንባታ ቁሳቁሶችን ድጋፍ ተደርገዋል።

ድጋፉን ያስረከቡት የገቢዎች ሚኒስትር ወ/ሮ ዓይናለም ንጉሴ፤ ተቋሙ ማኅበራዊ ኃላፊነቱን ከመወጣት አኳያ በርካታ ሥራዎችን እየሠራ ነው ብለዋል። ሚኒስትሯ ላለፉት አምስት ዓመታት በሀገር ደረጃ የመረዳዳት ባህል እና ማኅበራዊ ኃላፊነትን የመወጣት ተግባር እየተስፋፋ መምጣቱን ጠቅሰው ተቋሙ ከተሰጡት ገቢን የመሰብሰብ ኃላፊነት ጎን ለጎን ችግር ውስጥ ያሉ የኅብረተሰብ ክፍሎችን እምባ ያበሰ ሥራ መሠራቱን ገልጸዋል።

ክብርት ወ/ሮ ዓይናለም ንጉሴ፤ ድጋፉ እንዲደረግ ኃላፊነታቸውን ለተወጡ አመራሮች፣ ሠራተኞች፣ ግብር ከፋዮች እንዲሁም በሥራው ለተሳተፉ ሁሉ ምስጋና ይገባቸዋል ብለዋል። በተለይ ግብር ከፋዮች ግብራቸውን በታማኝነት ከመክፈል ባለፈ በዚህ መልካም ተግባር በመሳተፋቸው አመስግነዋል።

ወደ ገጽ 6 ዞሯል

# ከቢሊዮን ወደ ትሪሊዮን ጉዞን ዕውን ለማድረግ የገቢው ዘርፍ ተቋማት በቅንጅት መከሩ

**በሠሎሞን ወርቁ**



ሀገር አቀፍ የገቢው ዘርፍ ተቋማት የገቢ አሰባበሰብ ዋና ዋና ሥራዎች እና ዕቅድ አፈጻጸም የምክክር በድሬዳዋ ከተማ አካሄዱ።

የምክክር መድረኩን የከፈቱት የፌደራል የገቢዎች ሚኒስትር ክብርት ዓይናለም ንጉሴ፤ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ በምስራቅ አፍሪካ ትልቅ ኢኮኖሚ እንደሆነ አመልክተው ሆኖም ግን የሀገራችን ኢኮኖሚ ከሚያመነጨው ገቢ አኳያ አሁንም እጅግ አነስተኛ የታክስ ገቢ እየተሰበሰበ እንደሆነ ተናግረዋል።ይህንንም ለማሻሻል እና በገቢ አሰባሰቡ የላቀ ውጤት ለማምጣትም በተቀናጀ እና በተናበበ ሁኔታ መሠራት እንዳለበት ገልጸዋል።

በመድረኩ፤ የፌዴራል፣ የክልል እና የከተማ መስተዳደሮች ገቢ ተቋማት የግብር ከፋዮችን የታክስ ህግ-ተገዥነት ከጊዜ ወደ ጊዜ ማሻሻል እንደሚገባ እና በተጨባጭ እየተስተዋለ ያለው የታክስ ስወራ እና ማጭበርበር ልምምድን ለመቅረፍ የሚያስችል ሥራ ሊሠራ እንደሚገባ ተመክሯል።

ሁሉም የፌዴራል፣ የክልሎች እና የከተማ መስተዳደሮች የገቢ እቅድ አፈጻጸም የነበራቸውን ጠንካራ ጎኖች እና በተግባር የታዩ ክፍተቶች በመድረኩ የቀረቡ ሲሆን አፈጻጸሙ አበረታች በመሆኑ በቀጣይ የተለጠጠ እቅድ በማቀድ በሙሉ አቅም መሥራት እንደሚገባ ተነስቷል፡፡

የገቢ መጠንን ለማሳደግ ከታክስ መረብ ወጪ የሆኑትን ወደ ታክስ መረቡ ማስጋባት እና አዳዲስ ዘርፎችን ወደ ታክስ መረቡ እንዲካተቱ መደረግ እንዳለበት ሀሳብ ቀርቧል፡፡



ሚኒስትር ዴኤታ ክቡር አብዱርሃማን ኢድ ጣሂር፤

# የአፍሪካን ጉዳይ በአፍሪካውያን

**በሰሎሞን ደግአረገ**

የገቢዎች ሚኒስቴር በታክስ ኦፐሬሽን ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ ክቡር አብዱርሃማን ኢድ ጣሂር መሪነት አምስት አባላት ያሉበት የልዑካን ቡድን በኤክሳይዝ ታክስ ላይ ልምድ ካላው የኬንያ ገቢዎች ባለሥልጣን ጋር የልምድ ልውውጥ ከኅዳር 30 እስከ ታኅሣሥ 4 ቀን 2017 ዓ.ም በናይሮቢ አካሂዷል።

በአፈፃፀማቸው የተሻለ ደረጃ ላይ የደረሱ ሀገራትና ተቋማት ምርጥ ተሞክሮን በመለየት ከራስ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማስማማት አካትቶ መጠቀም ለአንድ ተቋም ስኬታማነት ከፍተኛ አስተዋጽዖ ስላለው የልምድ ልውውጡ በብሔራዊ የመካከለኛ ዘመን የታክስ ስትራቴጂ የተመለከቱ ኤክሳይዝ ታክስ አዋጅና የኤክሳይዝ ቴምብር

ወደ ገጽ 2 ዞሯል

# ርዕስ አንቀፅ



# ከቢሊዮን ወደ ትሪሊዮን

የገቢዎች ሚኒስቴር እና የጉምሩክ ኮሚሽን የገቢ አሰባሰብ አፈጻጸምን በማሻሻል እና ህገ-ወጥ ንግድን በመቆጣጠር በህግ የተሰጡትን ሥልጣንና ኃላፊነቶች በአግባቡ መወጣት የሚያስችሉ ስትራቴጂያዊ አቅጣጫዎችን በመከተል ተግባራዊ እያደረጉ ይገኛል፡፡

በዚህም መሠረት በሁሉም አካባቢዎች በኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ውስጥ ያሉ ግብር ከፋዮች ግዴታቸውን በአግባቡ እየተወጡ ስለመሆናቸው ማሳያ ሲሆን ችግር ሲያጋጥማቸው ችግራቸውን በባለቤትነት በመፍታት ሀገራችን ያላትን እምቅ የገቢ አቅም በብቃት በመሰብሰብ የመንግሥትን የልማት ፋይናንስ በጠንካራ መሰረት ላይ ማድረስ ከመቸውም ጊዜ በላይ ልዩ ትኩረት ይፈልጋል፡፡

ፌዴራል፣ ክልሎች እና ከተማ አስተዳደሮች ከዓመት ዓመት እያደገ የመጣ የገቢ አሰባሰብ ቢኖርም የሀገራችን ኢኮኖሚ ከሚያመነጨው ገቢ አንጻር አሁንም እጅግ አነስተኛ ነው፡፡ ምክንያቱም የኢትዮጵያ የታክስ ገቢ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ጋር ያለው ጥምርታ ከሰሃራ በታች ካሉ የአፍሪካ ሀገሮች ጋር በንጽጽር ሲታይ ገና ብዙ መሥራት ያለብን ጉዳይ እንደሆነ የተለያዩ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

ስለሆነም መንግሥት የሚጠበቅበትን ጠንካራ፣ ግልጽ እና ፍትሃዊ የገቢ ሥርዓትን በማጎልበት፤ ግብር ከፋዮችም ኃላፊነታቸውን እና መብታቸውን አውቀው ሀገር የምትጠብቅባቸውን በመወጣት ከቢሊዩን ወደ ትሪሊዩን የገቢ ጉዞ መሸጋገሪያ ስለሆነ በቁርጠኝነት የምንሥራበት ጊዜ ላይ ነን፡፡

ኢትዮጵያ የትሪሊዮን የሀገር ውስጥ ገቢ ጉዞዋን በትጋት እና በቅንጅት እውን እንዲሆን የሁላችንንም ያልተቆጠበ ጥረት የምትሻበት ጊዜ በመሆኑ መንግሥት ለገቢ አሰባሰቡ የታክስ ህግ ተገዥነትን ማረጋገጥ ላይ ትኩረቱን አድርጓል፡፡ የፌደራልና የክልል ገቢ ተቋማት የየራሳቸው ግልጽ ተልዕኮ ያላቸው ቢሆንም እንደ ሀገር ለላቀ ውጤት የሚያበቃ ሥራ ለመሥራት ተባብሮ መሥራቱ የግድ የሚልበት ጊዜ ነው፡፡

የግብር ከፋዮቻችን የታክስ ህግ ተገዥነት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለ የመጣ ቢሆንም በተጨባጭ እየተስተዋለ ያለው የታክስ ስወራ እና ማጭበርበር ልምምድ በቀላሉ የሚታይ አይደለም፡፡ ቁጥራቸው ቀላል የማይባል በኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ውስጥ ሆነው ግብራቸውን የማያሳውቁ፣ አሳንሰው የሚያሳውቁ፣ ባዶና ተመላሽ ማሳወቅ የዘወትር ተግባራቸው የሆነ አካላትን ሥራ ወሰን ሳይገድበን የመረጃ ልውውጥ በማድረግ ወደ ትክክለኛው የታክስ ሥርዓት በማስገባት የሀገራችንን ህልም ለማሳካት ይረዳናል፡፡

ይህንን ማድረግ ካልቻልን በገቢ አሰባሰቡ ላይ ከሚኖረው አሉታዊ ተጽዕኖ ባሻገር ህገ-ወጥነትን ያነግሳል፤ ለታክስ ሥርዓቱ ታማኝ ሆነው የሚሠሩትን ግብር ከፋዮች ገበያ ከፉኛ ይጎዳል፤ ከገበያም ያስወጣል፡፡ ስለሆነም የገቢዎች ሚኒስቴር እና የጉምሩክ ኮሚሽን ለገቢው ማደግ የሚጠበቅባቸውን ለመወጣት ከመቼውም ጊዜ በላይ ከክልል ገቢ ቢሮዎች ጋር በቅንጅት ለመሥራት ቁርጠኛ ሲሆኑ ግብር ከፋዮችም ህጋዊነትን ብቻ በመምረጥ ከቢሊዮን ወደ ትሪሊዮን ጉዞን ለማሳካት በቅንጅት እንዲሰራ የገቢዎች ሚኒስትር ክብርት ዓይናለም ንጉሴ መልዕክት አስተላልፈዋል፡፡

ገቢ ለልማት፤ በገቢዎች ሚኒስቴር የኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት የሚዘጋጅ ወርሃዊ ጋዜጣ

ዋና አዘጋጅ፡- ሰሎሞን ደግአረገ
ም/ዋና አዘጋጅ፡- ሰለሞን ወርቁ
አዘጋጆች፡- ሺመልስ ሲሳይ
እታገኝ አቦሰጥ
ጰሐፊና ሌይአውት ዲዛይነር፡- ብርሃኔ ሰለሞን
ፎቶግራፈር፡- ክፍሌ አዳፍሬ፣ እስካለም ሰፊው እና የትናየት እንዳያፍሩ
አድራሻ፡- ስልክ 11-6-17-84-90 ኮድ 2133 ፖ.ሣ.ቁ 2559
ዌብሳይት፡- www.mor.gov.et
ፌስቡክ Ministry of revenues of Ethiopia

የጋዜጣችን ውድ አንባቢያን፤ እንደምን ሰነበታችሁ? እንደተለመደው ጋዜጣችን ብዙ ጠቃሚ ሃሳቦችን ይዞ እንደቀረበ እየገለጽን ጥናትን መሠረት በማድረግ የጋዜጣውን ስም በፊት ወደ ነበረበት ከ’’ገቢያችን ጎልውናችን’’ ወደ ’’ገቢ ለልማት’’ የተመለሰ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

ስታክስ እና ስጉምሩክ ጉዳዮች መረጃ ነጻ ስልክ፡- 8199



# እንኳን ደስ አላችሁ!

የአዳማ እና የሀዋሳ ገቢዎች ግብር ከፋዮች ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች፣ የአዋሽ ጉምሩክ ቅ/ፅ/ ቤት የቢሮ፣ የሠራተኞች መኖሪያ እና የጉምሩክ መጋዘን ግንባታ፣ የጉምሩክ ኮሚሽን የኮምቦልቻ ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት እንዲሁም የገቢዎች ሚኒስቴር ዋና መሥሪያ ቤት የአራት ህንጻዎች ዕድሳት፣ የካፍቴሪያ ህንጻ ግንባታ ተጠናቀው ተመረቁ፡፡

በምርቃት ሥነ-ሥርዓቱ ላይ ንግግር ያደረጉት የገቢዎች ሚኒስትር ክብርት ዓይናለም ንጉሴ፤ የገቢዎች ሚኒስቴርና የጉምሩክ ኮሚሽን ዘመናዊ ኢትዮጵያን በመገንባት ሂደት የላቀ ሚና የነበራቸው ተቋማት መሆናቸውን ጠቁመው በአሁኑም ጊዜ መንግሥት ተልዕኮውን እንዲወጣ ገቢን በማመንጨት እና ህገ-ወጥነትን በመከላከል ተልዕኮአቸውን በላቀ ደረጃ በመፈፀም ላይ የሚገኙ ተቋማት መሆናቸውን አመልክተዋል፡፡

ሚኒስትሯ፤ የገቢ እቅድን ለማሳካት ምቹ፣ ዘመናዊ፣ ቀልጣፋ መጪውን ትውልድ ታሳቢ ያደረገ አገልግሎት መስጠት የሚያስችሉ መሠረተ ልማቶችን መገንባት ወሳኝ ሚና ያላቸው መሆኑን ጠቅሰው ሕንጻው ተመረቆ ለአገልግሎት ክፍት በመሆኑ የተሰማቸውን ደስታ ገልጸዋል፡፡ ሚኒስቴሩ ይህን ሥራ በሌሎች ቅርንጫፎችም እየሠራ ይገኛል ያሉት ሚኒስትሯ የ2017 በጀት ዓመት የገቢ እቅዳችንን ለማሳካት የምንመራበት መንገድ ከምን ጊዜውም የተለየ መሆን አለበት ብለዋል፡፡

የጉምሩክ ኮሚሽን ኮሚሽነር ደበሌ ቃበታ በበኩላቸው፤ ተቋማቱ በዘመን ብዛት የማይዋዥቁ እንዲሆኑ ለማስቻል በርካታ ሥራዎች እየተሠሩ መሆኑን ጠቁመው ህንጻዎች ተመርቀው ለአገልግሎት መብቃታቸው ለሀገራችን ኢትዮጵያ ብልፅግና እውን መሆን ፈተናዎችን አልፎ ማሸነፍ እንዲሁም ለማኅበረሰባችን በተጨባጭ ተጠቃሚ የሚያደርጉ ሥራዎችን መሥራት እንደሚቻል ማሳያ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ ኮሚሽነሩ፤ ከቢሮ ግንባታ ጎን ለጎን የአገልግሎት አሰጣጡ ዘመኑን የዋጀ እና በቴክኖሎጂ የታገዘ እንዲሆን በርካታ ተግባራት እየተከናወኑ ነው ብለዋል፡፡

በምረቃ መርሃ ግብሩ፣ የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱና የኮሚሽኑ አመራሮች እና ሌሎችም ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች የተገኙ ሲሆን ሥራው እንዲጠናቀቅ የበኩላቸውን አስተዋጽዖ ላበረከቱ አካላት እውቅና ተበርክቶላቸዋል፡፡

# የአፍሪካን ጉዳይ ...

ከገጽ 1 የዞረ

አስተዳደር ዙርያ መልካም ተሞክሮ መቀመርን ታሳቢ በማድረግ የተከናወነ እንደሆነ ሚኒስትር ዴኤታው ገልጸዋል፡፡

የአፍሪካን ጉዳይ በአፍሪካውያን መፍታት እርስ በርስ በመደጋገፍ ዘላቂ መፍትሄ ለማምጣት ስለሚረዳ በኤክሳይዝ ታክስ አዋጅና የኤክሳይዝ ቴምብር አስተዳደር ዙርያ ከሌሎች የአህጉሪቱ ሀገራት ውጤታማ የሆነውን የኬንያ ገቢዎች ባለሥልጣን ምርጥ ተሞክሮ ወደ ሀገራችን ለማምጣት ልምድ ቀስመናል ሲሉ የልዑኩ መሪ አሳውቀዋል፡፡

ልምድ ልውውጡ፤ ኤክሳይዝ ታክስ ቁጥጥር በማዘመን የሚሰበሰበውን የታክስ ገቢ በላቀ ሁኔታ ለማሳደግ ስለሚረዳ ለተቋማችን እጅግ ጠቃሚ ከመሆኑ ባሻገር የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱን የኤክሳይዝ ታክስ አሠራር ዓለም ከደረሰበት ደረጃ አንፃር በመፈተሽ ኋላቀር አሰራሩን በመለየት የተሻሻለ አሰራር ሊያመጣ የሚችል ስትራቴጂና ፕሮግራም ለመንደፍ ይረዳናል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የተሻሻለና ጥራት ያለው አገልግሎት ለግብር ከፋዮች ለመስጠት እንደሚያግዝም አቶ አብዱርሃማን ኢድ ጣሂር ተናግረዋል፡፡

# እንግዳችን



አዘጋጅ ሽመልስ ሲሳይ

# «በግብር ከፋዮች የሚቀርቡት ቅሬታዎች ፈጣን ምላሽ ማግኘት ይኖርባቸዋል»

- አቶ ደረጄ ፋና
በገቢዎች ሚኒስቴር የቀድሞ የታክስ ውሳኔ ቅሬታ ጽሕፈት ቤቶች ድጋፍና ክትትል ጽሕፈት ቤት ኃላፊ



**ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የሃገር ውስጥ ገቢን ለማሳደግ በርካታ ተግባራትን እያከናወነ ይገኛል። ከነዚህም ተግባራት መካካል በገቢዎች ሚንስቴር የግብር ከፋዮችን የታክስ ውሳኔ ቅሬታ ማጥራትና የቅሬታ አፈታት ሥርዓትን ማሳደግ አንዱ ነው። ይህንን አስመልክቶ ከቀድሞ የጽሕፈት ቤቱ ኃላፊ አቶ ደረጄ ፋና ጋር ቆይታ አድርገናል።**

**ጽሕፈት ቤቱ የግብር ከፋዮችን ቅሬታ የሚሰማበት ሂደቶች ምን ምን ናቸው?**

የቅሬታ ማጥራት የመጀመሪያ የሥራ ሂደት በታክስ አወሳሰኑ ላይ "ቅሬታ አለኝ" በሚል ማንኛውም ግብር ከፋይ ቅሬታውን በጽሑፍ ማቅረቡን መረጋገጥ ይኖርበታል። በቅሬታ አጠሪ ጽሕፈት ቤት የአሰራር መመሪያ እና በአሰራር ማንዋሉ በዝርዝር በተመለከተው መሰረት በግብር ከፋይ የሚቀርበው የቅሬታ ማመልከቻው ግልፅ እና በታክስ ውሳኔው ላይ በግብር ከፋይ ሊስተካከሉ ይገባሉ የሚላቸውን ዝርዝር ጉዳዮች የያዘ መሆን ይኖርበታል።

ከላይ በተጠቀሰው ሂደት የቅሬታ አጣሪ ጽሕፈት ቤቱ በግብር ከፋዩ የቀረበውን ቅሬታ በማጣራት ገምግሞ የቅሬታ ማመልከቻው በታክስ አስተዳደር አዋጅ መሠረት በአግባቡ የቀረበ ቅሬታ ከሆነ በቅሬታ አጣሪ ጽሕፈት ቤት መመሪያ በተመላከተው መሰረት ቅሬታውን ወደ ቀጣይ ደረጃ ይሸጋገራል በዚህም በጽሕፈት ቤቱ መመሪያ እና በሥራ ክፍሉ የአሠራር ማኑዋል መሠረት በታክስ ውሳኔ ላይ ቅሬታ የቀረበበት ውሳኔ ያስተላለፈው የሥራ ክፍል ለቀረበው ቅሬታ በጽሑፍ ምላሽ እንዲሰጥ ያደረጋል። ውሳኔውን ያስተላለፈው የሥራ ክፍል ምላሹን በጽሑፍ ከሰጠ በኋላ የቅሬታ አጣሪ ጽሕፈት ቤቱ ሁለቱን አካላት ፊት ለፊት በማገናኘት የአካል የቃል ክርክር በቅሬታው ላይ እንዲያደርጉ ያደረጋል።በክርክር ሂደቱም ጽሕፈት ቤቱ ያገኛቸውን ተጨማሪ ሃሳቦች በማደራጀት ለውሳኔ ሃሳብ በመረጃ በግብዓትነት ይጠቀማል።

**ጽሕፈት ቤቱ የግብር ከፋዮችን ቅሬታ እራሱ የመፍታት ኃላፊነት ተሰጥቶታል ወይ?**

በመጀመሪያ ደረጃ ግልጽ መሆን ያለበት ጉዳይ የቅሬታ አጣሪ ጽሕፈት ቤቱ ተግባር ከግብር ከፋዮች የቀረበውን ቅሬታ በህግ አግባብ ነፃ እና ገለልተኛ በመሆን ቅሬታውን አጣርቶ በቅሬታው ላይ በኃላፊ ለሚሰጠው ውሳኔ የውሳኔ ሃሳብ ማቅረብ ነው።ኃላፊው በጽሕፈት ቤቱ የቀረበውን የውሳኔ ሃሳብ በታክስ አስተዳደር አዋጅ 983/2008 አንቀፅ 55 (4) መርምሮ በቅሬታው ላይ የመጨረሻ ይሰጣል በመሆኑም በዚህ ሂደት የቅሬታ አጣሪ ጽሕፈት ቤቱ ኃላፊነቱ ቅሬታውን በማጣራት የውሳኔ ሃሳብ ማቅረብ ነው።

**በሚቀርቡት ምክረ-ሃሳቦች መሰረት ውሳኔ የሚሰጠው በሚኒስትር ብቻ ነው ወይ?**

የገቢዎች ሚንስቴር በአዲስ አበባ፣ በድሬደዋ እና በሌሎች ክልሎች ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች አሉት።በነዚህ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች ግብር ከፋዮች በታክስ ውሳኔ ላይ ቅሬታ ሲኖራቸው ወደ ዋናው ሚኒስቴር መሥሪያ ቤት መምጣት ሳይጠበቅባቸው ቅሬታቸውን በታክስ ከፋይነት በሚስተናገዱበት ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ማቅረብ ይችላሉ።በዚሁ አግባብ ይህም የቅርንጫፍ ሥራ አስኪያጁ በመመሪያ ቁጥር 171/20133 አንቀጽ 6 በተሰጠው ውክልና በቅሬታ አጣሪ ጽሕፈት ቤቱ ተጣርቶ በቀረበው የታክስ ውሳኔ ላይ መርምሮ ውሳኔ እንዲሰጥ ሥልጣን ተሰጥቶታል። በመሆኑም የቅሬታ አጣሪ ጽሕፈት ቤቶቹ ከላይ የዘረዘርኳቸውን ተግባራት እና ኃላፊነቶች ቅደም ተከተላቸውን ተከትለው በቅሬታው ላይ ለሚሰጠው የመጨረሻ ውሳኔ የውሳኔ ሃሳቦችን አደራጅተው ለቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶቹ ሥራ አስኪያጆች ያቀርባሉ።

**የግብር ከፋዮችን ቅሬታ ለማስተናገድ ታክስን አስመልክቶ በቂ ግንዛቤ ያስፈልጋል።ከዚህ አንጻር የጽ/ቤቱ ሠራተኞች ሙያዊ ስብጥር ምን ይመስላል?**

የገቢዎች ሚንስቴር ፍትሃዊ የታክስ አስተዳደር ሥርዓት በመገንባት ቀልጣፋ አገልግሎት አሰጣጥና የግብር አከፋፈል ሥርዓት እንዲፈጠር ጠንክሮ እየሠራ ይገኛል።ግብር ከፋዮች የሚያቀርቧቸው ከታክስ ውሳኔ ጋር በተያያዘ የሚያቀርቡ ቅሬታዎች በቅሬታ አጣሪ ጽሕፈት ቤቶች ከወገንተኝነት በፀዳ ሁኔታ በገለልተኛ ባለሙያዎች ተጣርተው ውሳኔ እንዲሰጥባቸው ለማድረግ ከፍተኛ ጥረት እያደረገ ይገኛል።ለዚሁም ሲባል የቅሬታ አጣሪ ጽሕፈት ቤቱ ባለሙያዎች የኢዲት፣ የህግ እና ከአካውንቲንግ ሙያ መስክ የተውጣጣ እንዲሆኑ ተደርጎ ሥራ ክፍሉን የማደረጃት ሥራ ተሠርቷል።በመሆኑ ጽሕፈት ቤቱ እነዚህን ልምድ እና ብቃት ያላቸውን ሠራተኞች ተጠቅሞ የቀረበውን የታክስ ውሳኔ ቅሬታ በማጥራት ውሳኔ እንዲሰጥ በማድረግ ሂደት ውስጥ ውጤታማ ተግባር እያከናወነ ይገኛል።

**ግብር ከፋዮች በተሰጠው ውሳኔ ላይ ቅሬታ ካላቸው በምን መልኩ ነው መስተናገድ የሚችሉት?**

በታክስ ውሳኔ ላይ በግብር ከፋይ ለቅሬታ አጣሪ ጽሕፈት ቤት ቅሬታ ቀርቦ በኃላፊ ውሳኔ ከተሰጠ በኃላ ግብር ከፋይ በቅሬታው ላይ የተሰጠው ውሳኔ ላይ "ቅሬታው አልተፈታም" ብሎ የሚያምን ከሆነ በህግ አግባብ በገቢዎች የተሰጠው ውሳኔ "የመጨረሻ ነው" ማለት አይደለም።ግብር ከፋዮች በተሰጠው ውሳኔ ላይ ይግባኝ የመጠየቅ መብት በህግ የተጠበቀ ነው።በቅሬታ በተሰጠው ውሳኔ የማይስማማ ማንኛውም ግብር ከፋይ በቅሬታ አጣሪ ጽሕፈት ቤቱ የውሳኔ ሃሳብ ቀርቦ በኃላፊ ውሳኔ የተሰጠበትን የታክስ ውሳኔ የፍሬ ግብሩን 50 በመቶ አስይዞ ወይም ከፍሎ በ30 ቀናት ውስጥ ቅሬታውን በታክስ አስተዳደር አዋጅ አንቀጽ 56 መሰረት ወደ ፌደራል ግብር ይግባኝ ኮሚሽን በመውሰድ ይግባኝ ማለት ይችላል።በህግ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ወይም መሰረት ወደ መደበኛ ፍርድ ቤቶች በመሄድ ይግባኝ ማለት ይችላል።

**ተጨማሪ መልዕክት ካለዎት?**

ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ግብር ከፋዮች የሚያቀርቡትን ቅሬታዎች የመስማት እና አጣርቶ በቅሬታው ላይ ውሳኔ መስጠት ኃላፊነት አለበት። በመሆኑም ቅሬታ የሚያቀርብ ማንኛውም ግብር ከፋይ ቅሬታውን በበቂ የሰነድ ማስረጃ አስደግፎ ማቅረብ ይኖርበታል።በታክስ አስተዳደር አዋጅ አንቀጽ 55 መሰረት በአግባቡ ያልቀረበ ቅሬታን ለማስተናገድ የቅሬታ አጣሪ ጽሕፈት ቤታችን ይቸገራል።ሌላው አጽንኦት ሰጥቼ ማሳሳብ የምፈልገው አቢይ ጉዳይ በታክስ ውሳኔ ላይ ቅሬታ የሚያቀርቡ ግብር ከፋይ ከቅሬታ ማመልከቻው ጋር አብሮ ደጋፊና አስረጂ የሂሳብ ሰነዶችን አያይዞ መቅረብ፣ የቅሬታ ሂደቱን የሚከታተል ብቁ ባለሙያ መመደብ ይኖርበታል።ከዚህም ባሻገር በተለያያ ከአቅም በላይ በሆነ ችግር "የቅሬታ ማቅረቢያ ቀን፣ የቅሬታ መስሚያ ቀጠሮ ይቀየርልን" በሚል ጥያቄ የሚያቀርቡ ግብር ከፋዮች ከህጋዊ የሰነድ ማስረጃ ጋር ከአቅም በላይ የሆነ ችግር የገጠማቸው ስለመሆኑ በማስረጃ በማስደገፍ፤ በማረጋገጥ ጥያቄያቸውን ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል። ይህ የማይሆን ከሆነ ጉዳዩ በጽሕፈት ቤቱ ሥራ ላይ ተጨማሪ ጫና ስለሚፈጥርና በቅሬታ አፈታት ሂደቱ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ስለሚኖረው መሰል ችግሮችን ግብር ከፋዮች ማረም መቻል አለባቸው።የታክስ ውሳኔ ቅሬታ ጽሕፈት ቤትም በግብር ከፋዮች ለሚቀርቡ ቅሬታዎች ፍትሐዊ፣ ገለልተኛ የሆነ አካሄድን በመከተል ፈጣን ምላሽ መስጠት ይጠበቅበታል።

**ገቢ ለልማት:-** አቶ ደረጄ ፋና ስለነበረን ቆይታ ከልብ አመሰግናለሁ።

**አቶ ደረጄ ፋና:-** እኔም አመሰግናለሁ።

2017 ዓ.ም

በነፃ የሚታደል

ገቢ ለልማት

ለግንዛቤዎ

አዘጋጅ ሠለሞን ወርቁ

# ከየካቲት 3 ቀን ጀምሮ ሙሉ በሙሉ ስለሚተገበረው ባለልዩ መለያ ደረሰኝ ምን ያህል ያውቃሉ?

ደረሰኝ በዕቃ ወይም በአገልግሎት ግብይት ላይ ተመስርቶ ከሻጩ/አቅራቢው ለገዥው የሚሰጥና ግብይት ስለመፈፀሙ፣ ገንዘብ ስለመሰብሰቡ፣ ዋጋው ስለመከፈሉ ወይም ለወደፊት ለመክፈል ውል መግባቱን የሚያሳይ ሰነድ ነው፡፡

በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ ከሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ ታትሞ የሚወጣ ደረሰኝ እና የማንዋል ደረሰኝ የሚባሉ ሁለት የደረሰኝ ዓይነቶች ያሉ ሲሆን በዚህ ጽሑፍ ትኩረት ነጥባችን የሚሆነው የሐሰተኛ ደረሰኝ ባህሪያትና የሚያስከትለው ጉዳት፣ ቀደም ሲል የታተመ ደረሰኝ እስከ መቼ መጠቀም እንደሚቻል እንዲሁም ከነበረው መመሪያ ምን እንደተሻሻለና የህትመት ሂደት በሚመለከት ከታክስ መረጃና የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ አስተዳደር ዳይሬክተር ተወካይ ወ/ሮ ዚነት አበጋዝ ጋር ቆይታ አድርገን እንደሚከተለው አቅርበናል፡፡



ወ/ሮ ዚነት አበጋዝ፤

## የሐሰተኛ ደረሰኝ ባህሪያት ምንድን ናቸው?

ከደረሰኝ ጋር ተያይዞ የሚፈፀሙ አገራዊ ገቢን የሚጎዱ ድርጊቶች ውስጥ ሽያጭን ለመደበቅ ሲባል ያለደረሰኝ ግብይት መፈፀም እና ወጪን ለማናር ወይም በግብዓት ላይ የሚከፈል የተጨማሪ እሴት ታክስ ለማናር ሀሰተኛ ደረሰኞችን መጠቀም ወይም ሀሰተኛ ግብይት መፈፀም ናቸው፡፡ እነዚህ ሀሰተኛ ደረሰኞች በባህሪያቸው የተለያየ ይዘት ያላቸው ሲሆን፡-

- በተቋሙ የህትመት ፍቃድ እንዲሰጣቸው ፍቃድ ከተሰጣቸዉ በኋላ ከ---እስከ ተብሎ የተፈቀደውን ደረሰኝ ተመሳሳይ ቁጥር በመጠቀም ድጋሜ /Double print/ በማሳተም ደረሰኙን ጥቅም ላይ ይውላል፤
- ከተቋሙ ፈቃድ ሳይሰጣቸው በህገ-ወጥ መንገድ ከማተሚያ ቤቶች ጋር በመመሳጠር እያሳተሙ የሚያሰራጭ፤
- በታክስ መረቡ ሳይገቡ በሥራ ላይ በሌሉ እና በማይታወቁ ሀሰተኛ ስሞች የታክስ መለያ ቁጥር እና ሀሰተኛ የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ ቁጥር ወይም የሌላ ድርጅት የተጨማሪ እሴት ታክስ ቁጥር እና የግብር መለያ ቁጥር በመጠቀም የሚዘጋጅ፤
- እንዲታተም በተቋሙ ተፈቅደው ከታተሙ በኋላ በቀሪና በበራሪ መካከል የዋጋ ልዩነት ተደርጎባቸዉ የሚሰሩዋቸው እንዲሁም
- የጠፉ ደረሰኞችንም ተጠቅመው የሚዘጋጁም ናቸው፡፡

## ሐሰተኛ ደረሰኝ ምን ጉዳት ያስከትላል?

### ሐሰተኛ ደረሰኝ የሚያስከት ለው ጉዳት ዘርፈ ብዙ ሲሆን ዋና ዋናዎቹ የሚከተ ሉት ናቸው:-

- ፍትሀዊ የንግድ ውድድር እንዳይኖር በማድረግ ህጋዊ ነጋዴዎች ከንግድ ሥርዓቱ እንዲወጡ ያደርጋል፤
- ያልተገባ ተቀናሽ እንዲደረግ ምክንያት በመሆን የመንግሥት ገቢን ያሳጣል፤
- የግብይት ተጨማሪ ዕሴት ታክስን በማጋነን በሽያጭ ላይ ከሚሰበሰበው ተጨማሪ ዕሴት ታክስ ላይ ያልተገባ ተቀናሽ ለማድረግ/ያልተገባ ተመላሽ ለመስጠት ዕድል ይሰጣል፣
- ሙስና እንዲስፋፋ ምክንያት ይሆናል፤
- ኮንትሮባንድ እንዲስፋፋ በር ይከፍታል፤
- በህጋዊ መንገድ የተሰበሰበው ታክስ በህገ-ወጥ መንገድ ከመንግሥት ካዝና እንዲወጣ ያደርጋል፤
- በተወሰኑ ችግር ፈጣሪዎች በሀቅ/በትክክል የሚነግዱትንና የሚያትሙትን ግብር ከፋዮች በጅምላ ስም እንዲጠፉ ያደርጋል፤
- ሀሰተኛ ደረሰኝ ተጠቅሞ የሚነግደው ቶሎ ስለማይደረስበት የሚጠበቅበትን ግብር አይከፍልም፣ በትክክል የሚሠራው ግብሩን በትክክል ስለሚከፍል በሚያገኘው ገቢ ማነስ ልዩነት ስላለው ቅሬታ ያስነሳል።

## አዲሱ የደረሰኝ ህትመት ምን አዲስ ነገር ይዞ መጥቷል?

የደረሰኝ ህትመት በአንድ ማተሚያ ቤት የተለያዩ ምስጥራዊ መለያ ኮዶች ያሉትና በቴክኖሎጅ የተደገፈ ሆነው እንዲታተም ሚንስቴር መ/ቤቱ የክልሎችንና ከተማ አስተዳደሮችን ጭምር ኃላፊነት ወስዶ ስምምነቱ የሁለትዮሽ በመሆኑ ሁለቱም ተቋማት የሚጠበቅባቸውን ኃላፊነት በግልና በጋራ ለመወጣት የሚያስችል፣ ለተመረጠው ማተሚያ ቤት ከፍተኛ ኃላፊት የሰጠ፣ ከሀሰተኛ የታክስ ደረሰኝ ህትመትና ስርጭት ጋር እንደ ሀገር የሚስተዋሉ ችግሮችን ለመቀነስ እና በቀጣይ አሰራሮችን በማሻሻል ለማጥፋት የሚያስችል በመሆኑ ከቀድሞው አሰራር ለየት ያደርገዋል፡፡

## አዲሱ የደረሰኝ ህትመት ምን ዓይነት ችግሮችን ይቀርፋል?

### ባለልዩ መለያ የደረሰኝ ህት መት የሚከተሉትን ችግሮች ይቀርፋል:-

- በየትኛውም የሀገሪቱ ክልል በአንድ ማተሚያ ቤት ታትሞ እንዲሠራ መሆኑ ለቁጥጥር ምቹ ነው፤
- ለአንድ አታሚ ድርጅት ብቻ እንዲያትም በመደረጉ ክፍተት ሲኖር ለማረም፤ ጥፋት ሲኖር ተጠያቂ ለማድረግ ቀላል ነው፤
- ህትመቱን ከፍቃድ እስከ ህትመት እንዲሁም ከስርጭት በኋላ አጠቃቀሙን የመከታተል እና ቁጥጥሩ በሲስተም/በቴክኖሎጂ የተደገፈ በመሆኑ በቀላሉ የማይቀየሩ ስለሆነ ችግሩን ይቀንሰዋል፤
- ልዩ መለያ ያለው የታክስ ደረሰኝ ህትመት መሆኑ በሞባይል እስክሪን ተደርጎ ከሚነበበዉ በተጨማሪ ምንም በቀላሉ በዓይን፤ በሞባይል ስልክ የማይታይ ልዩ ኮድ ያለው መሆኑ እና በቀላሉ ሊደረስበት የማይችል መሆኑ ልዩ ያደርገዋል፤
- የደረሰኝ ዓይነቶች መለያየት እንጅ ደረሰኝ ህትመት አንድ ቦታ መሆኑ ከዚህ ወጣ ያለ ደረሰኝ ጥቅም ላይ የማይውል እና ተቀባይነት እንደሌለው በመመሪያ መደንገጉ፤
- ወጥ የሆነ አሰራር በሀገር ደረጃ እንዲኖር በመደረጉ ህገ-ወጥ ደረሰኝን በከፍተኛ ሁኔታ ለመቀነስ ያስችላል፤
- የደረሰኝ ቁጥጥሩ በቀጣይ በሚዘረጋው አሰራር በቴክኖሎጅ የተደገፈ መሆኑ ችግሩን ይቀርፋል ተብሎ ይታመናል፤
- ግብር ከፋዩን ከአላግባብ ወጭ ለመታደግ ህትመት ፈቃድ የሚጠይቁ ግ/ከፋዮች ከምልልስ የሚያድን / እንግልትን የሚቀንስ መሆኑ እና ችግር ቢፈጠረ ጥያቄውን የሚያቀርበው ፈቃድ በጠየቀበት ቦታ ብቻ መሆኑ እና ለፍትሀዊ ግብር ከፋዮች ከመጭበርበር የመዳኛ ዘዴ ነው፡፡

## አዲሱ የደረሰኝ ህትመት ምን ዓይነት ይዘቶች አሉት?

### ባለልዩ መለያ የደረሰኝ ህት መት የሚይዘው ይዘት የሚከ ተሉት ናቸው:-

- በአንዳንዱ ደረሰኝ ቅጠል ላይ የተለያየ QR code እና ልዩ ምስጥራዊ ኮድ ያለው መሆኑ፣
- የQR code በታክስ ደረሰኙ በቀኝ በኩል መሆኗ እና 2በ2 ሴንቲሜትር መሆኑ፤
- የሚጠቀመዉ ቀለም ink jet መሆኑ፤
- ለደረሰኙ የወረቀት እስታንደርድ 60 መሆኑ እንዲሁም
- የግብር ከፋዮች መረጃ በተወሰኑ አካላቶች ብቻ በመሆኑ ምስጢራዊነታቸው የሚጠበቅ መሆኑ፣ ምስጢር ከወጣ ተጠያቂነት ያለው ነው፡፡

## ቀደም ሲል የታተመ ደረሰኝ እስከ መቼ መጠቀም ይቻላል?

ግብር ከፋዩ ቀድሞ ያሳተመውን የታክስ ደረሰኝ እስከ የካቲት 2 ቀን 2017 ዓ.ም የመጠቀም መብት አለው፡፡ ነገር ግን ከየካቲት 3 ቀን 2017 ዓ.ም ጀምሮ ስለሚያስወግድ እና አዲሱን QR code ያለውን የታክስ ደረሰኝ ስለሚጠቀም ከታህሳስ አንድ ጀምሮ ቀድሞ ያሳተመው የደረሰኝ ህትመት ካቆመበት የደረሰኝ ቁጥር ቀጥሎ ያለውን ለጊዜው መሥሪያ ከሌለው በተለመደው ጠይቆ በማሳተም ቀጣዩን ቁጥር ለብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት እንዲታተምለት በማድረግ በወቅቱ ደረሰኙን በእጅ መያዝ አለበት፡፡

በተለያየ የንግድ ሥራ ላይ የተሰማሩ የንግድ ማህበረሰብ የሚጠበቅባቸውን የታክስ ግብር በወቅቱ አሳውቆ የመክፈል ግዴታቸውን መወጣት አለባቸው፡፡ ነጋዴው ማኅበረሰብ ደረሰኝ የመቁረጥ ግዴታው የመወጣት እና ያለ ደረሰኝ ግብይት ባለመፈጸሙ ህገ-ወጥ ተግባርን በጋራ መከላከል አለበት፡፡ ታክስን የሚሰውር /የሚያጭበረብር/ ደረሰኝ የማይቆርጡ የንግድ ማህበረሰብን በመጠቆም ወደ ሥርዓቱ እንዲገቡ ማድረግ ይገባል፡፡ ማኅበረሰቡም ለሚፈጽመው ግዥና ለሚጠቀመው አገልግሎት ደረሰኝ የመቀበል ኃላፊነቱን በመወጣት ደረሰኝ የማይሰጥ ካለ በመጠቆም ህግን በጋራ ማስከበር አለበት፡፡

## ግብር ከፋዩ የታክስ ደረሰኝ ህትመት ፈቃድ ለመጠየቅ ሲመጣ ምን ማሟላት አለበት?

### ደረሰኝ ለማሳተም፤


- ሙሉ አድራሻ፡- ስም፣ ቀበሌ /ወረዳ፣ ዞን፣ ክ/ከተማ፣ የቤትና ስልክ ቁጥር ማስመዝገብ አለበት፤
- የታደሰ ንግድ ፈቃድ የመያዝ፣ የግብር መለያ ቁጥር፣ የንግድ ስም፣ የንግድ አድራሻና ቅርንጫፍ ካለው የሁሉንም ዝርዝር ማስመዝገብ አለበት፤
- ሌሎች ተጨማሪ የሚያስፈልገውን መረጃ በመመሪያ ቁጥር 149/2011 ላይ ከተገለፁት የሚመለከተውን ማሟላት፣ ማቅረብና ማስመዝገብ አለበት፤

አንድ ግብር ከፋይ የታክስ ደረሰኝ ከብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት እንዲታተምለት ግብር በሚከፍልበት ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ተገኝቶ የህትመት ትዕዛዝ ማቅረብ ይችላል፡፡ በአንድ የሚያዝዘው ዝቅተኛው የፓድ/የጥራዝ/ ብዛት 5 ሲሆን እስከ 300 ፓድ ማዘዝ ይችላል፡፡ የጥራዙን ብዛት ዋጋ በአቅራቢያ ባለ የንግድ ባንክ በተከፈተው የማተሚያ ቤቱ አካውንት በማስገባት ደረሰኙን ኮፒ በማድረግ ሁለቱንም ይዞ ታክስ /ማዕከሉ/ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት በመሄድ ማዘዝ እና የታዘዘበትን ቁጥር ይዞ ህትመቱ ሲደርስ፡-

- አዲስ አበባ ያሉ የፌደራል ስድስቱ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች እና የአዲስ አበባ የከተማ አስተዳደር ገቢዎች ቢሮ ስር ያሉ የሁሉም ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች ግብር ከፋዮች የከፈለበት ደረሰኝና ማንነታቸውን የሚገልጽ መታወቂያ ይዘው ማተሚያ ቤት በመሄድ ለህትመት የጠየቁትን የደረሰኝ ዓይነት ጥራዝ እና ለህትመቱ የከፈሉበትን ደረሰኝ አስቆርጠው መውሰድ አለባቸው፡፡ ከ3000 ብር በላይ ከሆነ ለደረሰኝ ህትመቱ የከፈሉት 2% የዊዝ ሆሊዲግ ደረሰኝ ቆርጠው ለማተሚያ ቤቱ መስጠት አለባቸው፡፡
- ከአዲስ አበባ ውጭ የሚገኙ የፌደራል ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች፣ የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ቢሮ እና የ12 ክልል ገቢዎች ቢሮ በሲስተም ለህትመት የተጠየቀው የግብር ከፋይ ደረሰኝ ታትሞ መጠናቀቁ መረጃ ሲደርሳቸው ህትመት የተጠየቀበት ዝርዝር የግብር ከፋዩ መረጃ እና የደረሰኝ ዓይነቶቹን የሚገልጽ በሰንጠረዥ የተዘጋጀና ለባንክ ገቢ ያደረገበትን ደረሰኝ ኮፒ እንዲሁም የሚወስደውን አካል/ሰው የሚገልጽ ደብዳቤ በመስጠት እንዲወሰድ ሲመጣ ለእያንዳንዱ ግብር ከፋይ ለታክስ ደረሰኝ ለህትመት ለከፈለው ብር ከማተሚያ ቤቱ ደረሰኝ አስቆርጦ በመውሰድ ለግብር ከፋዩ ከደረሰኙ ጋር ማሰራጨት አለበት፡፡ ግብር ከፋዩ ከ3000 ብር በላይ ከሆነ ለደረሰኝ ህትመቱ የከፈለው 2% የዊዝ ሆሊዲግ ደረሰኝ ቆርጠው ለማተሚያ ቤቱ እንዲላክ ለቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቱ ለግብር ማዕከሉ መስጠት አለበት፡፡

ወደ ገጽ 6 ዞሯል


# በየዓይነቱ




አዘጋጅ እታገኝ አቦሰጥ

በሰሎሞን ደግአረገ


## ሰዎች ስለግብር ምን አሉ?





## እንቆቅልሽ ሳይ እንዴት ናችሁ?


### ግብር የመክፈል ኃላፊነት አለብኝ፡፡ እኔ ማን ነኝ?



መልሱን ታውቁታላችሁ? በ0116178490 (2133) አጋሩን፡፡

## አውታረ-መረብዎ (Network) ከሳይበር ጥቃት ምን ያህል የተጠበቀ ነው?

ደህንነቱ የተጠበቀ አውታረ-መረብ (Network) የማንኛውም ተቋም የሳይበር ደህንነት ስትራቴጂ የጀርባ አጥንት ነው፡፡ ይህን ለማረጋገጥ ግን ከመሠረታዊ የደህንነት እርምጃዎች በዘለለ አጠቃላይ የደህንነት ተግባራትን መከወን ይጠይቃል፡፡ደህንነቱ የተጠበቀ አውታረ-መረብ (Network) ለመገንባት ተግባራዊ ልናደርጋቸው የሚገቡ 9 ነጥቦች፡-




እነዚህ እርምጃዎች እያንዳንዳቸው ለሳይበር ጥቃት የማይበገር የመከላከያ ስርአት ለመፍጠር ወሳኝ ሚና ይጫወታሉ፡፡
ተቋምዎ እስካሁን ከእነዚህ እርምጃዎች ውስጥ የትኞቹን ተግባራዊ አድርጓል?
ምንጭ፡-የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር

# የግብር ቱርፋቶች



የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የኮሪደር ልማት



የሀዋሳ ከተማ አስተዳደር የኮሪደር ልማት፣




የሶዶ ከተማ የኮሪደር ልማት



የሐረር ከተማ የኮሪደር ልማት




የባሕር ዳር ከተማ የኮሪደር ልማት




የቢሾፍቱ ከተማ የኮሪደር ልማት



የጅማ ከተማ የኮሪደር ልማት




የአርባ ምንጭ ከተማ የኮሪደር ልማት



የሸገር ከተማ የኮሪደር ልማት

# «...ታዋቂዎችም...

ከገጽ 8 የዞረ

መረዳት የተቻለው ይህን ያህል የግብር ገንዘብ አለመክፈላቸው ገቢን በዲጂታል መንገድ ተከታትሎ ማስከፈል ላይ ክፍተት መኖሩን ነው፡፡

ዋና ዳኛ ፖል ጎልድስፕሪንግ በዌስት ሚኒስተር ማጅስተርስ ፍርድ ቤት፣ ‹‹ውስብስብ የፋይናንሺያል ማትሪክስ የሚመስል ቀጥተኛ የገቢ ማጭበርበር ነው›› በማለት የጥፋተኛነት ብይን ሰጥቷል።

ቀደም ሲል በተደረገ ችሎት ሳራ ክላርክ ኬሲ የተባሉ ዳኛ፤ የቀድሞ ኪክ ቦክሰኞች የነበሩትን ወንድማማቾች፣ ‹‹ተከታታይ ግብር እና የተጨማሪ እሴት ታክስ አጭበርባሪዎች ናቸው›› በማለት ገልጸው ነበር።

የዚህን ወንጀል ጉዳይ የሰሙ ባለሥልጣናት፤ ‹‹ማንም ሰው፤ ተጽዕኖ ፈጣሪዎችም ወይም ታዋቂዎችም ቢሆኑ ከሕግ በላይ አይሆኑም›› ሲሉ መልእክታቸውን አስተላልፈዋል።

ተከሳሾቹ በአሁኑ ጊዜ ሮማኒያን ለቀው እንዳይወጡ ቢታገዱም የፍርድ ሒደቱ ከተጠናቀቀ በኋላ እ.ኤ.አ ከ2012 እስከ 2015 እንደፈጸሙ የተጠቀሰባቸውን የአስገድዶ መድፈር እና የሰዎች ዝውውር ተጨማሪ ክሶች ለመከታተል ለዩናይትድ ኪንግደም ተላልፈው ተሰጥተዋል።

የሚገርመው፤ ሩማንያ ውስጥ በሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር፣ አስገድዶ መድፈር እና ሴቶችን ለመበዝበዝ ያለመ የወንጀል ድርጅት በማቋቋም ክስ የቀረበበት አንድሪው ቴት፤ ‹‹እንግሊዝ ስኖር ግብር ለመክፈል ፈቃደኛ አልነበርኩም›› ሲል በድፍረት መናገሩ ሲሆን የርሱም ሆነ የወንድሙ ድርጊት በሕዝብ ዘንድ ያላቸውን ክብር እና ተቀባይነት አውርዶባቸዋል።

**ምንጭ ፡-** የቢቢሲ እ.ኤ.አ ኦገስት 22/2024 እና የስካይ ኒውስ ዲሴምበር 18/2024 ዘገባ

# በቆጠራ ያልተደገፈ፣...

ከገጽ 8 የዞረ

ከፋብሪካው መዝገብ ዋጋ 174 ሚሊዮን ብር ጋር ሲነጻጸር 20 በመቶ በታች ነው። ስለሆነም ወጪው የዕቃ መሸጫ ዋጋ ግንባታ አካል መሆን አለበት እንጂ የቋሚ ዕቃ ባህሪ ያለበት ነው ተብሎ የመሸጫ ዋጋ ማሳነስ እንደማይገባ ግብር አስከፋዩ መስሪያ ቤት ተከራክሯል።

ድርጅቱ ከውጪ አገር ለማስገባት አወጣሁ የሚለው ወጪ ከፋብሪካው መዝገብ ዋጋ ጋር ሲነጻጸር ከ20% በታች መሆኑን አይክድም። ድርጅቱ ባቀረበው ክርክር በአዋጁ ከ20% በታች ከሆነ ደግሞ በገቢ ግብር ዓዋጅ ቁጥር 287/1994 አንቀጽ 23/11 ላይ በተገለጸው አግባብ እርጅናውን ቅናሽ ከፍ ለማድረግ የሚል ሲሆን የምምረቻ ወጪ በወጪነት ሊያዝ የሚገባው ነው።

በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀፅ 23/11 መሰረት ለማምረቻ ማሽኖች የወጡ የጥገናም ሆነ የማሻሻያ ወጪዎች እንደማምረቻ ወጪ እንደሚያዙ ተደንግጓል። ይህ ድንጋጌ ከቋሚ ዕቃዎች ዋጋ አንጻር ሲታይ ከ20% በላይ ሆነው የቋሚ ዕቃው አካል በመሆን የእርጅና ቅናሽ የተሰላለት የቋሚ ዕቃው አካል በመሆን የገቢ ግብር ዓዋጁ በሚፈቅደው መሰረት እንደሚቀናነስ የሚያሳይ ነው። መለዋወጫ ዕቃዎቹ የቋሚ ዕቃዎቹ አካል ሲሆኑ ለረጅም ጊዜ የሚያለግሉ በመሆናቸው ከጥገና ወጪነት ወደ ቋሚ ንብረትነት የሚያደሉ ናቸው።

በመሆኑም ድርጅቱ ያቀረባቸው መከራከሪያዎች የህግ ስህተት ያለባቸው በመሆኑ የገቢዎች ሚኒስቴር ድርጅቱ ግብር እና ታካስ እንዲከፍልባቸው ባለባቸው ጉዳዮች ላይ ድርጅቱ እንዲከፍል የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔውን አስተላልፏል።

**ምንጭ:-** በገቢዎች ሚኒስቴር ሕግ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት

# ከ140 ሚሊዮን ብር...

ከገጽ 1 የዞረ

የጉምሩክ ኮሚሽነር ደበሌ ቃበታ በበኩላቸው ከለውጡ ማግስት ጀምሮ ማኅበራዊ ኃላፊነታችንን ለመወጣት በርካታ ቁሳቁሶች ድጋፍ መደረጉን ጠቅሰው ወደፊትም ይህ ተጠናክሮ ይቀጥላል ብለዋል። ድጋፉን የተረከቡት አመራሮች ድጋፉ እየተከናወነ ላለው ዕድገት ከፍተኛ እገዛ እንደሚያደርግ ገልጸው በችግራችን ጊዜ ከጎናችን በመሆን ስላበረታችሁን እናመሰግናለን ብለዋል።

# ከየካቲት 3 ቀን ጀምሮ ሙሉ በሙሉ ስለሚተገበረው ...

ከገጽ 8 የዞረ

- የአንድ ጥራዝ ደረሰኝ ዋጋ 450 /አራት መቶ አምሳ/ ብር ሲሆን VAT 15% እዚሁ ተካቷል። 2% ዊዝ ሆልዲግ ኦን ፓይመንት እና 7.5% ቫት ዊዝ ሆልዲግ የሚመለከታቸው በታክስ አስተዳደር እና በኤክሳይዝ ታክስ አስተዳደር አዋጁ መሰረት ተፈፃሚ በማድረግ ደረሰኝ በመቁረጥ ለብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት እንዲደርሰው አዲስ አበባ ያለ ግብር ከፋይ ራሱ/ወኪሉ ደረሰኙን ሲያመጣ መስጠት አለበት፣ ክልል ላይ የሚገኙ የፌደራል ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች፣ የክልል ገቢዎች ቢሮ እና የድሬደዋ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ቢሮ ደረሰኙን ከግብር ከፋዩ በመቀበል ለማተሚያ ቤቱ መላክ አለባቸው።

የታክስ ደረሰኝ ህትመቱን የሚያትመው የማተሚያ ድርጅቱ ስም ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፣ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር- 0000007141 ሲሆን የደረሰኙ ዋጋ ገቢ የሚደረግበት የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የባንክ ሒሳብ ቁጥር 1000003794141 ነው። በህጉ ደረሰኝ እንዲያሳትሙ የሚገደዱ ሁሉም የፌደራል፣ የከተማ አስተዳደርና የክልል ግብር ከፋዮች አዲሱን የደረሰኝ ህትመት ለማሳተም ግብር የሚከፍልበት ታክስ ማዕከል ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት በመሄድ የህትመት ጥያቄ ከወዲሁ ማቅረብ አለባቸው፤ ምክንያቱም ለህትመት ሥራውና ለስርጭቱ ጊዜ መስጠት ስለሚያስፈልግ። በህጉ ደረሰኝ እንዲያሳትሙ የሚገደዱ ሁሉም የፌደራል፣ የከተማ አስተዳደርና የክልል ግብር ከፋዮች ከየካቲት 3/2017 ዓ.ም ጀምሮ አዲሱን QR Code ያለው ደረሰኝ ሥራ ላይ የማዋል ግዴታ አለባቸው።

## በመሬት መንቀጥቀጥ ጊዜ መደረግ ያለባቸውን ጥንቃቄዎች ያውቃሉ?



በተለያየ ምክንያት ከቤት ውጭ ከሆኑ፡- ከዛፎች፣ ከሕንጻዎች፣ ከኤሌክትሪክ ምሦሶዎች እና ሌሎች ወድቀው ጉዳት ሊያደርሱ ከሚችሉ ነገሮች መራቅ እና ገላጣ ሜዳ አካባቢ መሆን ይመከራል።

በቤት ውስጥ ከሆኑ፡- በበር መቃኖች፣ ኮርነሮች እና ኮሪደሮች ተጠግቶ ማሳለፍ እንዲሁም ከእሳት ምድጃዎች፣ ከተሰቀሉ ፍሬሞች እና የግድግዳ ጌጦች፣ ከመጽሐፍ መደርደሪያዎች ፣ ከመስኮት አካባቢ መራቅ እና የጋዝ ምድጃዎችን በተቻለ ፍጥነት ማጥፋት ካልሆነም ከአካባቢው መራቅ።

በትልልቅ ሕንጻዎች ውስጥ ከሆኑ፡- ከሕንጻዎቹ ለመውጣት አለመሞከር፣ አሳንሰር (ሊፍት) በፍፁም አለመጠቀም። ከደረጃዎች አካባቢ መራቅ።

መኪና እያሽከረከሩ ከሆኑ፡- የኤሌክትሪክ መተላለፊያ ምሦሶዎች፣ ዛፎችና ሽቦዎች አካባቢ አለመቆም፣ የኤሌክትሪክ መስመር ምሦሶዎች እና ሽቦዎች ተሽርካሪው ላይ ከወደቁ ከመኪናው ለመውጣት አለመሞከር፣ በተቻለ ፍጥነት ገላጣ ወደሆነ አካባቢ መኪናን ማቆም እና መሰል የጥንቃቄ መንገዶችን መከተል እንደሚገባ የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ኢንስቲትዩት መክሯል።

# The Willingness ...

Continued from page 7

social, and environmental growth through increased income are being viewed positively.

She underscored the crucial role domestic revenue plays in achieving these objectives. “To realize this The EU is willing to assist this initiative and has requested the appropriate support from the ministry.

# “Executing ...

Continued from page 7

The delegation of the World Bank, Mr. Rajul Awatshi, said that the Ethiopian government has premeditated to boost domestic revenues. To realize this ambition, executing excise tax principles will play a significant role, and the World Bank will deliver the necessary support to the Government of Ethiopia, according to Mr. Rajul.

During the occasion, key issues on excise administration modalities and options, and implementation of new administrative arrangements were presented by the delegations of the World Bank and discussed by the participant.

# The Ministry ...

Continued from page 7

Speaking at the event, Minister of Revenues H.E. Mrs. Aynalem Nigussie highlighted that; Ethiopia’s membership in the BRICS family would enhance its access to more economic opportunities, drive growth, and address development challenges.

“The agreement outlines a strategic partnership that will positively impact collecting domestic revenue using digital tax transformation”, and the minister expressed her absolute gratitude to the delegation for sharing their insights and commitment to this strong partnership.

Head of International Cooperation Directorate, Federal Tax Service of Russia, Mr. Elisey Balta on his side, said that domestic revenue is a significant source of funding for governments.

The Ethiopian government is doing encouraging activities, to boost the domestic revenue, and the Federal Tax Service of Russia is willing to share its experience of digital tax transformation, according to the director.

# Ministry of ...

Continued from page 7

ambitious vision, the Ministry of Revenues has been implementing various initiatives, with strong partnerships being a cornerstone of our success. The newly launched project must operate with discipline, guided by strategic policies, and leverage technology as a critical enabler while avoiding duplication,” said Ms. Aynalem.

Senior Advisor and Project Lead of Tony Blair Institute for Global Change (TBI) Ms. Sinit Zeru emphasized the long-term vision of the initiative. “This project seeks to empower the Ministry of Revenues to leverage digital transformation effectively, increasing its revenue collection capacity to fund Ethiopia’s developmental goals,” she said.

The project, set to run 2025 to 2026, focuses on creating a sustainable institutional ecosystem to enhance revenue collection efficiency. The two-year initiative is designed to achieve four key outcomes and deliver 13 strategic objectives, positioning the Ministry as a modernized, tech-driven institution capable of meeting Ethiopia’s economic aspirations.

# TIPS



አዘጋጅ Shimelis Sisay



## The Willingness of the European Union to support the Revenue Sector

The Ministry of Revenues has discussed with the European Union delegations. The discussion was held at MOR head office in December 2024.

At the occasion, Mr. Osman Mohammed, director of strategy and partnership, emphasized that the Ministry of Revenues is one of the giant ministries working with different stakeholders. Among those stakeholders' development partners are the prime ones. From the development partners, the European Union is the major one.

Working with the European Union plays a pivotal role in boosting domestic revenues and the ministry will deliver the necessary support accordingly, he added.

Mr. Maxime Heyndrickk, the delegation of the European Union in Ethiopia, stated that the Ethiopian government's efforts to promote inclusive and sustainable economic,

Continued on page 6

## The Ministry of Revenues (MOR) and the Russian Federal Tax Service signed a Memorandum of Understanding (MOU)

The main aim of the memorandum is to promote partnerships and to share the experience of Digital Tax Transformation.

The MOU was signed by Her Excellency Mrs. Aynalem Nigussie, Minister of Revenues, and Mr. Elisey Balta, Head of the International Cooperation Directorate, Federal Tax Service of Russi on Dec 2024 at MOR head office.

Continued on page 6



## Ministry of Revenues Launches Digital Transformation Project in Partnership with TBI and BMGF



The Ministry of Revenues (MOR) has officially launched the Digital Transformation Project in collaboration with the Bill & Melinda Gates Foundation (BMGF) and the Tony Blair Institute for Global Change (TBI). The initiative aims to modernize revenue collection and enhance Ethiopia's fiscal capacity to support its ambitious development goals.

Speaking at the kick-off event, Minister of Revenues H.E. Ms. Aynalem Nigussie highlighted the government's extensive reform activities over the past five years, which have been pivotal in driving rapid and inclusive economic growth.

Continued on page 6

## "Executing Excise Principles will Play a Significant role in Boosting the Domestic Revenues."

The World Bank

The Ministry of Revenues, Customs Commission, and World Bank held discussions on the excise tax issue in Addis Ababa.

Continued on page 6



# ሕግ - ግብር



አዘጋጅ ሠለሞን ወርቁ

# በቆጠራ ያልተደገፈ፣ ግዥን በማሳነስ ማሳወቅ እና ብክነትን አለማሳወቅ ያስከተለው ቅጣት

ዴይ ላይት አፕላይድ ቴክኖሎጂስ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ቆርኪ አምራች ድርጅት ነው። ለዚህም ድርጅቱ በቆጠራ ያልተደገፈ በእጅ ያለ ዕቃ ወደ ሽያጭ ተቀይሮ ግብር መክፈል እንዳለበት፤ የቀረበ የቆርኪ ምርት ልዩነት እና ብክነትን በተመለከተ ተሰልቶ ግብር እንዲከፈልበት እንዲሁም ከ2007 እስከ 2009 ዓ.ም ድርጅቱ ከውጪ አገር የመለዋወጫ ዕቃዎች ግዥን ወጪ በእርጅና ቅናሽ በመያዙ "በወጪ እንጂ በእርጅና ቅናሽ አትይዝም" ተብሎ በሕጉ መሰረት ክስ ቀርቦበታል።

የገቢዎች ሚኒስቴር የክሱን መሰረት ያደረገው በአዋጅ ቁጥር 979/2008 አንቀጽ (63) (1) (መ) መሰረት አንድ ግብር ከፋይ በግብር ዓመቱ መጨረሻ በግብር ከፋይ እጅ የሚገኙ የንግድ ዕቃዎችን ዓይነት መጠን፣ ዋጋ እና የዋጋ መገመቻ ዘዴን የሚያሳይ ሰነድ አዘጋጅቶ የሒሳብ መዝገቡ ሪፖርት መዘጋጀት እንዳለበት እና ድርጅቱ የደረጃ "ሀ" ግብር ከፋይ በመሆኑ የሚያቀርበው የሒሳብ ዝርዝር ሰነድ ተገቢውን የሒሳብ አዘገጃጀት መርሕን ተከትሎ ሪፖርቱን አዘጋጅቶ ማቅረብ እንዳለበት ይጠበቃል። በዴይላይት አፕላይድ ቴክኖሎጂስ ኃ/የተ/የግ/ማህበር ግን በ2007 ዓ.ም እና በ2008 ዓ.ም በሒሳብ መግለጫ ላይ የተገለጸው እና በዓመቱ መጨረሻ በእጅ ላይ የቀረው ጥሬ ዕቃ መጠን መካከል ልዩነት እንዳለ እና በቆጠራ ያልተደገፈ ዕቃ በድርጅቱ እጅ ተገኝቷል። ይህ ደግሞ በውጪ ኦዲተሮች ከተረጋገጠው ጥሬ ዕቃ ለምርት ጥቅም ላይ እንደዋለ ተደርጎ በመያዙ እና የተስተካከለ ሪፖርት ባለማቅረቡ ድርጅቱ 2,598,411.52 (ሁለት ሚሊዮን አምስት መቶ ዘጠና ስምንት ሺ አራት መቶ አስራ አንድ ብር ከአምሳ ሁለት ሳንቲም) ላይ ግብር እና ታክስ ሊከፍል እንደሚገባ ጠይቆታል።

ድርጅቱ የ2007 ዓ.ም እና የ2009 ዓ.ም ኦዲት ተደርጎ ሪፖርት ቀርቦበታል። በሪፖርቱ መሰረት የኢንቬንተሪ ዋጋው 14,808,595.00 ብር እና በዚሁ ጊዜ በሰነድ የቀረበው ደግሞ 13,685,511.86 ብር በመሆኑ በኢንቬንተሪ ዋጋው እና በቀረበው ሰነድ መካከል ያለው ልዩነት 1,123,083 ብር ሆኗል። ይህንን ልዩነት በ2008 ዓ.ም እንደገና በመጻፍ እና ሁለት ጊዜ በመደመር 2,598,411.52 ብር ወጪ ማድረጉን በመግለጽ እንደወጪ እንዲያዝለት፣ የቆርኪ ምርት ብክነት እንዳለ ታስቦ እንዲያዝለት እና ከውጪ አገር ያስገባቸው የመለዋወጫ ዕቃዎች ግዥ እንደ ወጪ እንዲያዝለት ለገቢዎች ሚኒስቴር አቤቱታ አቅርቧል።

ዴይላይት አፕላይድ ቴክኖሎጂስ ኃ/የተ/የግ/ማህበር በበኩሉ በ2008 ዓ.ም በመነሻው ላይ ያለው 13,22,180.69 ብር የሚቀነስ በመሆኑ መጠየቅ ያለበት 1,276,236.84 ብር ጋር ተደምሮ ሳይሆን ተቀንሶ ነው። ልዩነቱ በሙሉ ሽያጭ ነው ቢባል እንኳን እንደትርፍ ሊወሰድና ሙሉ ለሙሉ ግብር ሊታሰብበት አይገባም። ግብር ሊታሰብ ነገር ግን ድርጅቱ ለተለያዩ የለስላሳ ምርቶች ጠርሙስ ክዳን ቆርኪ የሚያመርት ሲሆን በ2009 ዓ.ም 6,187,980.20 ብር የምርት ልዩነት እንዳለው ተደርጎ ግብር የተወሰነበት የመጀመሪያው ጉዳይ በአመቱ መጨረሻ ያላለቀ (work in process) ላለው ከመዝገብ ዋጋ ላይ ያለውን ዋጋ በአንድ የጥሬ ዕቃ ነጠላ መግዣ ዋጋ (unit cost) በማካፈል እንጂ በቆጠራ የነበረውን የTIN Free Sheet ጥሬ እቃ ወስዶ ባለመሆኑ የምርት ልዩነት ሊመጣ እንደቻለ ያነሳል።

በሌላው ክስ ላይ በማነስ የተገለጸ የውጪ አገር ግዥን በተመለከተ ሲሆን ድርጅቱ ከ2007 እስከ 2009 ዓ.ም ከውጪ አገር የተለያዩ ግዥዎችን በመፈጸም ወደ አገር ውስጥ አስገብቷል። አብዛኞዎቹ ግዥዎች ለምርት ግብዓት የሚውሉ ሳይሆኑ ለቋሚ ንብረቶች፣ የማሽን መለዋወጫዎችና የማሽን መትከያ አገልግሎት፣ የመለዋወጫ ዕቃዎች አካል በመሆናቸው፣ ለጥሬ ዕቃ ግብዓት ባለመሆናቸው የቋሚ ዕቃ አካል በመሆናቸው ክፍያዎች በመሆናቸው የውጪ አገር ግዥን በማሳነስ የ2,178,576.71 ብር ልዩነት አለው። በገቢ ግብር ሕጉ እና በገቢ ግብር ደንብ መሰረት ከንብረቱ የመዝገብ ዋጋ ከ20% በታች ያለው መለዋወጫ ዕቃ ዋጋ የማምረቻ ወጪ ሆኖ በወጪነት የሚያዝ ሲሆን ከንብረቱ የመዝገብ ዋጋ ከ20% በላይ ያለው የመለዋወጫ ዕቃ ዋጋ ደግሞ የቋሚ ዕቃው አካል ሆኖ የእርጅና ቅናሽ እንደሚያዝለት ተቀምጧል። ድርጅቱ ከውጪ አገር ገዝቶ ያስገባቸው የመለዋወጫ ዕቃዎች ዋጋ ከቋሚ ንብረት የመዝገብ ዋጋ 20% በታች መሆኑ የታመነ ሲሆን በኦዲት ጊዜም ተረጋግጧል። የእነዚህን ዕቃዎች ዋጋ ወጪ የምርቱ የመሸጫ ዋጋ በሚያመጣበት ጊዜ የዋጋው ግንባታ አካል ማድረግ ይገባው ነበር ይህን ባለማድረጉ የዕቃዎች ዋጋ በማነስ እንዲውቁት አድርጎታል። የማሽን መለዋወጫ ግዥ (የጥገና ወጪ) ከ20% ከማሽኑ ያነሰ ከሆነ በወጪ ይካተታል።

የቋሚ ዕቃዎች መለዋወጫ ዋጋ ከቋሚ ዕቃ ዋጋ 20 በመቶ በታች በሚሆንበት ጊዜ ወጪው በወጣበት ግብር ዘመን የሚመረት ዕቃ መሸጫ ዋጋ ግንባታ መሆን እንዳለበት ይታመናል። ድርጅቱ እነዚህን ዕቃዎች ለቆርኪ ማምረቻ ፋብሪካ የተጠቀመባቸው መሆኑን አይከድም። ይህ ወጪ በ2008 ዓ.ም

ወደ ገጽ 6 ዞሯል

# «...ታዋቂዎችም ቢሆኑ...!»

በእስክንድር መርሐጽድቅ


ኤሞሪ አንድሪው ቴት እና ታናሽ ወንድሙ ትሪስታን ቴት የተወለዱት በአሜሪካ ነው። ሁለቱም ከወላጆቻቸው ጋር የከፋ ችግርን አሳልፈዋል፡፡ ሆኖም ግን በጊዜ ሒደት አንድሬው ቴት የተዋጣለት ቦክሰኛ ሆኖ አራት ጊዜ የኪክቦክስ ዓለም ሻምፒዮን ለመሆን በቅቷል፡፡ ይህ ብቃቱ እና ዝናው የሀብት መጠኑን እያሳደገው ሔዶ 33 እጅግ በጣም ፈጣን የቅንጦት መኪኖች እንዲሁም የግል ጀቶች እና ጀልባዎች ባለቤት አድርጎታል፡፡

ትሪስታን ቴት ደግሞ እንደ ወንድሙ ወደ ስኬት ለመምጣት የታደለው የኪክ ቦክሰኛ፣ የቴሌቪዥን ተዋናይ እና በኢንተርኔት የኦንላይን ፋንስ ቢዝነስ አንቀሳቃሽ ሆኖ ነው፡፡

ትሪስታን ቴት ለመጀመሪያ ጊዜ ታዋቂ የሆነው እ.ኤ.አ. በ2011 በብሪቲሽ የቴሌቪዥን ትርዒት ላይ በሠራው ሥራ 500 ሚሊዮን ዶላር የተጣራ ትርፍ አግኝቶ ነበር፡፡ የሩማንያ ካሲኖ ፍራንቻይዝ እና ከ10 ሚሊዮን ዶላር በላይ ወርሃዊ ገቢ የሚያስገኙለት በርካታ ኩባንያዎችም አሉት።

ሁለቱም በስኬት ላይ ስኬትን እየጨማመሩ ሲጓዙ ግን ከ2014 እስከ 2022 ካገኙት ከ21 ሚሊዮን ፓውንድ ገቢ ላይ የሚጠበቅባቸውን ከሁለት ሚሊዮን ፓውንድ በላይ ግብር ባለመክፈላቸው ተከሰዋል። ክሱ የቀረበለት ፍርድ ቤት የተከሳሾቹን በሰባት ባንኮች ላይ የነበሯቸውን ከታክስ ጋር የተገናኙ የባንክ ሒሳቦች አግዷል።

ከታገደው የተከሳሾቹ የባንክ ሒሳብ በተጨማሪ በአራት ንብረቶች ላይ ለ10 ሠዓታት በተደረገው ፍተሻ 16 የቅንጦት መኪናዎችቻቸው የተያዙ ሲሆን ገንዘብ እና ሌሎች ቁሳቁሶች፣ የቅንጦት ሰዓቶች፣



ከግራ ወደ ቀኝ ትሪስታን ቴት እና  አንድሪው ቴት

ላፕቶፖች፣ ሃርድ ዲስኮች እና ሰነዶች በቁጥጥር ስር ውለዋል።

በፍርድ ቤቱ የተደመጠው አስተያየት እንደሚያመለክተው፤ ወንድማማቾቹ ያን ሁሉ ሀብት ያፈሩት የሚፈለግባቸውን ግብር በተከታታይ ባለመክፈላቸው ነው፡፡ ከዚህ

ወደ ገጽ 6 ዞሯል

**የገቢዎች ሚኒስቴር ራዕይ**

በ2022 ዘመናዊ የታክስ አስተዳደር ተገንብቶ ሀገራዊ ወጪ በታክስ ገቢ ተሸፍኖ ማየት

**እ ሴ ቶ ች**

1. አገልጋይነት (Customer centric)
2. ሙያዊ ብቃት (Professionalism)
3. በቡድን መሥራት (Team work)
4. መሰጠት (Dedication/commitment)
5. ታማኝነት (Loyality)



በታክስ እና በጉምሩክ
ጉዳዮች ላይ
መረጃ ለማግኘት
ወደ8199
ነጻ የጥሪ መስመር
ይደውሉ
8199
SAMSUNG
የገቢዎች ሚኒስቴር
Ministry of Revenues